## ሾሌ ያ ነጭ ጠላ
## ለታላቁ አድባር ለታላቁ ጥላ

ጥላሁን ያ ጥላ ሁን
ከየት እናገኝህ አሁን
ማን ያጥላልን በዚህ ዘመን
እንዲያው ሃምሳ አመት መዝፈን
እስር ጨለማ ብርሃን
ሲፈራረቁብህ አልፈህ ሁሉን።

ምን ያረጋል ሞት አይቀር
ቀድመህ ብለሃል ደጋጉን ቢያስቀር
አንተም አንዱ ነበርክ ከሚቀሩት
ለኢትዮጵያ ብለው ከኖሩት።

ቢለወጥ ሞት-ተራ ለሚወዱት
ለጥላሁን ነበር የኔ ህይወት
ግን አይቀርም ዕልፈት
ተለየን ከጥላሁን ድንገት።

ሾሌ ያ ነጭ ጠላ
ለታላቁ አድባር
ላታላቁ ጥላ

ከእቾክ እችክ እስከ ኡኡታ አያስከፋም
ከእይዋት ስትናፈቀኝ እስከ ከመለያየት ሞት ነው
ከምክሬን ስምኝ እስከ እንጉዳዬ ነሽ
ከልጅቷ እስከ ኩሉን ማን ኳለሽ።

ካንዱ ቀን እስከ እያሳቀችኝ
ካራዊቱ እስከ የህይወቴ ህይወት
ካሳለፍነው እስከ የጥንቱ ትዝ አለኝ
ከምኞቴ ተሳካ እስከ አባት ደስ ይለዋል
ይህን ሁሉ ፀጋ ማን ያገኘዋል።

ካመልካች ጣት እስከ ሩቅ ምስራቅ
እንዲህ እንደ አሁኑ ሳንራራቅ
ከሰፊው ህዝብ እስከ ነገሥታት
ሾሌ ያ ነጭ ጠላ ዝንት ዓመታት

ከሌሊት ጨረቃ እስከ ዐይኔ ሁልጊዜ
ከዘምባባ ዛፍ ነሽ እስከ ሞና ሊዛ
ዘፈን እንደ አሁኑ ሳይንዛዛ
ሙዚቃው ጣዕም ያለው ለዛ
አሳልፍነው በዋዛ ፈዛዛ።

ከዋይ ዋይ ሲሉ እስከ ግፉ በለው
ካገር የጋራ ነው እስከ አገር አለኝ
ሾሌ ያ ነጭ ጠላ ለጥላሁን
የማይሰለች እስከ አሁን።
ከምግብ አይነቶች እስከ እንቁጣጣሽ
ከዘንድሮ እስከ ምን ታደርጊዋለሽ
የታሰረበት ሶስት አልማዞች።

እማይሰለች እማይጠገብ
መድረክ አይበቁ ስግብግብ
በላንቃ ድምጽ በቲያትር
ባይን ጥቅሻ ሁለ ገብ።

ካገር ፍቅር ብሔራዊ
ኦልኬስትራ ኢትዮጵያ
ከሁሉ ሰርቶ ከባለ ሙያ
ካድናቆት በላይ ለሁሉ መለኪያ።

ከስግብግብ ጆሮዬ ለዕውነት እሞታለሁ
ከባለ ጠላ እስከ ሁሉን አይቼዋለሁ።
ትቶልን ካለፈው ይሁነኝ ማልቀሻ
ዘላላም እንዲሆን ለኛ ማስታወሻ።

ተጠልቶ ያልቃል ወይ አባይን በጭልፋ
የጥላሁን ስራ ኦሜጋና አልፋ
ልሰናበተው እንግዲህ በይፋ
ለዘላለሙ እሱም ያንቀላፋ

በአርካን ፋኔ በሾሌ ያ ነጭ ጠላ
ለታላቁ አድባር ለታላቁ ጥላ

**ክንፈ ሚካኤል**
**ሚያዝያ ፲፭ ቀን ፪ ሺህ አንድ ዓ/ም**